# ለዘላቂ የኢትዮጵያ ህልውና፣ ሰላምና እድገት ዋስትና የሚሰጥ በአል

## ክፍል ሁለት

ለሚ ዋቄ 12-17-14

በዚሁ ርዕስ በቀረበ ክፍል አንድ ፅሁፍ ላይ 9ኛው የኢትዮጰያ በሄሮች፣ በሄረሰቦችና ሕዝቦች በዓል መከበርን ተከተሎ የተሰነዘሩ አስተያየቶችን ጠቅሼ በተለይ "የብሄሮች፣ በሄረሰቦች መብት እስከመጨፈር" በሚል የተሰነዘረ ቧልትን መነሻ በማድረግ አሰተያየት ሰጥቼ ነበር ያበቃሁት። በዚህ ክፍል ሁለት ፅሁፍ ደግሞ በክፍል አንድ መግቢያ ላይ የጠቀሰኩትን በአዲሰ አድማስ ሳምንታዊ የአማርኛ ጋዜጣ ነፃ አስተያየት አምድ ላይ "የ 'ብሔር ብሔረሰቦች በዓል' ፋይዳው ምንድን ነው?" በሚል ርዕስ በባዩልኝ አያሌው የቀረበ ፅሁፍ ላይ የሰፈረውን ሃሳብ እንመለከታለን። ከዚሁ ጋር በማያያዘ የዘንደሮው በአል የተከበረበት የቤኒሻንጉል ጉምዝ ህዝብ ስሜትና የክልሉን ምንነት በእጭሩ እንመለከታለን።

ፀሃፊ ባዩልኝ አያሌው የዘንድሮው ብሄሮች፣ በሄረሰቦችና ሕዝቦቸ ቀን በተከበረበተ ሰኞ ህዳር 29 ማለዳ ህፃናትና ወጣት ተማሪዎች የብሄሮች ብሄረሰቦችን ማንነት የሚያንፀባርቅ ባህላዊ አለባበስን መነሻ በማደረግ የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ቀን መከበሩየሃገር አንድነት ያናጋል በሚል እንዳሳሰባቸው ነው የነገሩን። ፀሃፊ ባዩልኝ የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች በአለባበስ ብቻ ሳየሆን በቋንቋና በታሪክም የተለያዩ መሆናቸውን ቢያስታውሱ መልካም ነበር።

ፀሃፊ ባይለየኝ ያሳሰባቸው የተለያዩ ብሄራዊ ማንነቶች ጎለተው መውጣታቸው ነው። ይህ "አንድነትን የማናጋት አደጋ ያስከትላል" ባይ ናቸው። እንደፀሃፊው እምነት ልዩነቶቻችን በአንድ በግድ በተጫነ መለያ መሸፈን ነበረበት። ለዩነቶች ተደፈቀው ሁሉም ከፍቃዳቸው ውጭ የሚያመሳስላቸውን የራሳቸው ያልሆነ የማንነት መገለጫ ሊጫንባቸው ይገባል ባይ ናቸው። የባዩልኝ አንድነት የዚህ አይነት የግዳጀ አንድነት ነው።

ይህ አመለካከት ከሃያ አመታት በፊት የኢትዮጲያ በሄሮች፣ በሄረሰቦችና ሕዝቦች የህይወት ምስዋእትነት ከፍለው የገረሰሱት አሃዳዊ ስርአት አመለካከት ነው። የኢትዮጵያ በሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የቀደመውን አሃዳዊ ስርአት አስወግደው፣ ብሄራዊ ልዩነታቸውነ እንደጠበቁ በመከባበርና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የህዝቦች አንድነት ከመሰረቱ ከሃያ ዐመታት በላይ አስቆጥረዋል። ራሳቸውን በራሳቸው እያሰተዳደሩ በልዩነት የገነቡት አንድነት ምንም የመገነጣጠል ስጋት አላስከተለም። አነዲያውም ሰላምና ልማትን በማፋጠን በኢኮኖሚ በማሰተሳሰር ምንም እርስ በርስ መጠራጠር የሌለበት ጠንካራ አንድነት ነው የፈጠረው። ፃሃፊ ባዩልኝ የሚናፍቁት ለብሄራዊ ማንነት እውቅና ነፈጎ በወሰን አንድነት የጨፈለቀ አሃዳዊ ስርአት በየአቅጣጫው የበሄራዊ ነፃነት የትጥቅ ትግል በመቀሰቀስ ሃገሪቱን ወደመገነጣጠል አፋፍ ወሰዶ እነደነበረ መታወስ ይኖረበታል።

እናም ፀሃፊ ባዩልኝ አሁን ስላለው የህዝቦች አንድነት ምንም የማያውቁ በሆነ አጥር ከነባራዊው እውነታ ተከልለው የተቀመጡ ሰው ናቸው። አለያም የኢትዮጲያ በሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ማንነታቸው ህጋዊ እውቅና ተነፈጎት በማንነታቸው እንደ ሁለተኛ ዜጋ እነዲታዩ፣ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዘቦች ላይ ባእድ ማንነት ተጭኖ በማንነታቸው እንዲሸማቀቁ የተደረገበትንና የህዝብ ሳይሆን የወሰን አንድነት የነበረበትን ስርአት ናፋቂ ናቸው። ይህ ከቀደሞት ስርአቶቸ አመለካከተ ውረዴነት የመነጨ የፀሃፊው ሃሳብ ዳግም ላይመለሰ የተቀበረ ሙት ነው።

ሞቶ የተቀበረው የቀደሞው አሃዳዊ ስርአት ናፋቂዎች ምንም አሉ ምን፣ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ በሄረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በመላው የኢትዮጵያ በድምቀት ተከብሯል። በተለይ የሁሉም በሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ተወካዮች በተገኙበት ቤኒሻንጉል ጉምዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መዲና አሶሳ በአሉ በለዩ ድምቀት ተከብሯል።

ለመሆኑ የቤኒሻንጉለ ጉምዝ ክልል ህዝብ ማነው? የቤኒሻንጉለ ጉምዝ ክልል በሰተምስራቅ ከኦሮሚያ፣ በስተምእራብ ከደቡብ ሱዳን በስተደቡብ ከጋምቤላ፣ በስተሰሜን ከአማራ ክልል ጋር የሚዋሰን ክልል ነው። የቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል የአምስት ብሄረሰቦች መኖሪያ ነው። እነዚህም የበርታ፣ የጉምዝ፣ የባሮ ሺናሻ፣ የማኦና ኮሞ በሄረሰቦች ናቸው።

የክልሉ በሂረሰቦች በዘውዳዊውውና በወታደራዊ ደርግ የመንግስት ስርአቶች አናሳ የዜግነት መብት እንዳላቸው ተደረጎ ነበረ የሚቆጠሩት። ብሂረሰቦቹ ለማንነታቸው እውቅና ተነፈጎት በእውነተኛ መጠሪያቸው ሳይሆን፣ የብሂረሰቦቹ አባላት የማያውቁት የማነቋሸሻ ማንነት ተለጠፎባቸው ነበር የሚጠሩት። በብሂራዊ ማንነታቸው ከሚደርስባቸው ጭቆናና መገፋት ጋር ለአሰከፊ ኢኮኖሚያዊ ጨቆናም ተዳርገው ነበር። የቤኒሻንጉለ ጉምዝ ብሂረሰቦች ባለፉት ስርአቶች እንደ ሕዝብ - እነደ ሰው ምንም ዋጋ አልተሰጣቸውም ነበር።

የዘውዳዊው ስርአት ነገስታትና መሳፍንት እንዲሁም ዘውዳዊውን ስርአት የተካው ወታደራዊ ቡድን፣ አፄ መኒሊክ ግዛታቸውን በሃይል አስፋፍተው በስተምእራብ ከእንግሊዝ ሱዳን ጋር እስከተዋዋሉት ወሰን ድረስ ላለው መሬትና የተፈጠሮ ሃብት እንጂ ለክልሉ ብሂረሰብ ብሂራዊ፣ ሰብአዊና ደሜክራሲያዊ መብትና ነፃነት እንዲሁም የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ቅንጣት ታህል ዋጋ አልሰጡም ነበር። ለእነዚህ ገዢዎች በአካባቢው ግኡዝ መሬት እንጂ፣ መብታና ነፃነት፣ ጥቅምና ፍላጎት ያለው ሕዝብ አልነበረም።

በዚህ ምክንያት በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል የሚኖሩት አምስቱ በሂረሰቦች እነደሰው ሳይቆጠሩ የማነቋሸሻ ሰያሜ ተለጥፎባቸው፣ የተቀሩት የኢትዮጲያ ብሂሮች፣ ብሂረሰቦችና ሕዝቦች ሳየቀሩ በትክክለኛ ማንነታቸው ሳያወቋቸው የሰው ልጅ ስልጣኔን ያህል እድሜ ባስቆጠረ እጅግ ኋላ ቀር የኑሮ ዘይቤና አሰከፊ ድህነት ውስጥ ለመኖር ተገደዋል። ይሁን እነጂ የቤኒሻንጉል ጉምዝ በሂረሰቦች እነደተቀሩት ለጭቆና ተዳርገው የነበሩ የኢትዮጵያ ብሂሮች፣ ብሂረሰቦችና ህዝቦች ሁሉ ጭቆናውን በፀጋ አለተቀበሉም። አናም ይህን ዝንተ አለም በኖሩበት ምድር ላይ እነደሰው እንዳይታዩ ያደረጋቸውን ስርአት ባልተደራጀና በተደራጀ አኳኋን ታግለዋል።

የዘንድሮው የብሂሮች፣ በሂረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በቤኒሻንጉለ ጉምዝ ክልላዊ መንግስት መከበሩን ምክንያት በማደረግ ህዳር 28፣ 2007 ዓ/ም በአሶሳ ከተማ በተዘጋጀ አውደ ጥናት ላይ “የኢፌዴሪ ሕገመንግስትና የቤኒሻንጉለ ጉምዝ ሕዝቦቸ ታሪክና ተጠቃሚነት” በሚል ርዕስ በቀረበ ጠናታዊ ፀሁፍ ብሂረሰቦቹ ለመብትና ለነፃነታቸው ያደረጉትን ትግል ይገልፃል። በጥናታዊ ፀሁፉ መሰረት የቤኒሻንጉል ጉምዝ ብሂረሰቦች ለነፃነታቸው መከበር

የተደራጀ የትጥቅ ትግል የጀመሩበትንና በአዲሲቱ ኢትዮጵያ ምስረታ ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ የገልፃል።

ጥናታዊ ፀሁፉ በቤኒሻንጉል ጉምዝ የነበረውን ሁኔታ አስመልክቶ " . . . ያለፉ ጨቋኝ ስርአቶች ሁሉንም የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የልማት፣ የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት ጥያቄዎቻቸውን የረገጡና ያፈኑ መሆናቸውን ሁሉም የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ሃይሎች የሚገነዘቡት ሃቅ ቢሆንም፣ በተለየ የቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል ህዝቦች ያሳለፉት ጭቆና ግን እጅግ የከፋና የተደራረበ ነበረ ማለት ይቻላል።" ይላል።

ጥናታዊ ፅሁፉ አያይዞም "የክልሉ ነባር ብሄረሰቦች ተወላጆቸ ለከፋ የድህነትና ኋላቀረነት የተዳረጉ ከመሆናቸውም በላይ፣ ማንነታቸው ተረግጦና በመልካቸውና በቆዳ ቀለማቸው የተነሳ ሌላ ሰም እየተሰጣቸው ተንቀውና በማነነታቸው ተሸማቀው፣ ከነባር ይዞታቸውም ተገፍተው ለሰው ልጅ ኑሮ መቹ ባልሆኑ ቆላማና ጠረፋማ አካባቢዎቸ ለመኖር የተገደዱ ሲሆን፣ ያልተሰደዱት ደግሞ ያለማንነታቸው የሌሎችን ማንነት ተላብሰው በሃገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ተበታትነው ለመኖር የተገደዱ ሕዝቦች ነበሩ። በመሆኑም፣ እነዚህ ለበርካታ አመታት የተከማቹ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች እንዲሁም የብሄር፣ ብሄረሰቦች የማንነት ጥያቄዎችን ለመፍታት ከሌሎች ወገኖች ጋር በመሆን በተደራጀና ባልተደራጀ መልኩ ለዘመናት ሲታገሉ ቆይተው በከፈሉት መስዋዕትነት ለዛሬው ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ስርአት በትግላቸው ሊበቁ ችለዋል።" ይላል።

ይህ በጥናታዊ ፅሁፉ የተገለፀ እውነታ የማያውቅ ኢትዮጵያዊ አለ ማለት አይቻልም። አስመሳዮች አለያም የቤኒሻንጉል ጉምዝ ብሄረሰቦች አሁንም የነበሩበት ጭቆና ውስጥ እንዲኖሩ የሚፈልጉና ከሕዝብ ይልቅ የወሰን አንድነት እንዲመሰረት የሚመኙ ካልሆኑ በስተቀር።

ከላይ የጠቀስነው ጥናታዊ ፅሁፍ የቤኒሻንጉል ጉምዝ ብሄረሰቦች ያካሄዱትን የትግል እንቅስቃሴ አስመልክቶ "የክልሉ ነባር ብሄረሰቦች ተወላጆች በተለያዩ የተቃውሞ አደረጃጀቶች እየተሳተፉ በግልና በተናጥል በሁሉም አካካቢዎች ሲደረግ የነበረው ትግልና መስዋእትነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በ1970ዎቹ እንቅስቃሴ የጀመረውና በዋናነት የበርታ

ብሄረሰብ ተወላጆችን ያሰባሰበው 'የቤኒሻንጉል ሕዝብ ነፃነት ንቅናቄ' በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ሃይሎች ድጋፍ በ1981 ዓ/ም ተመስርቶ በ1982 ዓ/ም የትጥቅ ትግል በመጀመር ለአፋኙና ለአምባ ገነኑ የደርግ ስርአት መደምሰስ የራሱን አስተዋፅኦ አድርጎ የሽግግር መንግስት ከመሰረቱት የፖለቲካ ድርጅቶች አንዱ ለመሆን በቅቷል።" ሲል ይገልፃል።

ይህ እውነታ አምባገነኑ የደርግ መንግስት ማንነታቸው እውቅና ተነፍጎት ለብሄራዊ ጭቆና በተዳረጉ በሄሮች፣ በሄረሰቦችና ሕዝቦች ባካሄዱት የነፃነት ትግል መገርሰሱን እንዲሁም አዲሲቱን ኢትዮጵያ የመመሰረት ተልዕኮ የነበረውና በኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ተሳትፎ የኢፌዴሪ ህገመንግስት እንዲዘጋጅ ያደረገው የሽግግር መንግስት ደርግን ለውድቀት ባበቁ የብሄራዊ የነፃነት ግንባሮች የተመሰረተ መሆኑን ያረጋግጣል። የአዲሲቱ ኢትዮጵያ የሉአላዊ ስልጣን ባለቤቶች በመራራ ትግል ነፃነታቸውን የተጎናፀፉ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች መሆናቸውን ያሳያል።

የቤኒሻንጉል ጉምዝ በሄረሰቦች ለነፃነት ያደረጉትን ትግልና በአዲሲቱ ኢትዮጵያ ምስረታ ውስጥ ያላቸው ድርሻ ላይ ጥናታዊ ፅሁፉ ላይ ከተገለፁት እውነታዎች፣ ከላይ የተጠቀሰውን ያህል እስታውሼ በመቀጠል በዚሁ ጥናት ላይ በአዲሲቱ ኢትዮጳያ ውስጥ ያገኙዋቸውን ፋይዳዎች አስመልክቶ የተገለፀውን ወደመመልከት ለሻገር።

ጥናታዊ ፅሁፉ ከቤኒሻንጉል ጉምዝ ሕዝብ ጋር በተያያዘ ከደርግ መገርሰስ በኋላ በአዲሲቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ሁኔታ አስመልክቶ " አምባገነኑ የደርግ ስርአት ከተገረሰሰ በኋላ የክልሉ ሕዝቦች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መበቶቻቸው ሕገመንግስታዊ ዋስትና በማገኘቱ፣ በብሄራዊ ማንነታቸው ተደራጅተው የራሳቸውን ክልላዊ መንግስት በመመሰረት ራሳቸውን በራሳቸው የማሰተዳደር፣ ክልላቸውን የማልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ማፋጠን፣ የመሰረተ ልማት፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማረጋገጥ አዲስና ታሪካዊ ጉዞ የተያያዘበተና ሕዝቦች በተጨባጭ ተጠቃሚ መሆን የጀመሩበት ሁኔታ ተፈጥሯል። በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ የተመዘገቡት የልማትና መልካም አስተዳደር ስኬቶች የክልሉ ሕዝቦች ለዘመናት ከነበሩበት ኋላቀርነትና የእድገት ደረጃ አንፃር ሲታይ ታሪካዊና እመርታዊ ነው ማለት ይቻላል።" ሲል ይገልፃል።

ጥናታዊ ፅሁፉ በኢፌዴሪ ሕገመንግስት በተፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎች የተገኙ ዴሞክራሲያዊና የሰብአዊ መብት፣ የፍትህ፣ የመልካም አስተዳደር ስኬቶች ይዘረዝራል። ከዚህ በተጨማሪ በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ የተገኙ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ስኬቶች ቀደም ሲል ከነበረው ጋር በመነፃፀር ያሳያል። ለዚህ ፀሁፍ ዓላማ ጥናቱ በቤኒሻንጉል ጉምዝ ተመዘገቡ በሎ ከገለፃቸው የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማቶች መሃከል የተወሰኑትን እጠቅሳለሁ።

እጅግ ኋላ ቀር በነበሩት የቤኒሻንጉል ጉምዝ ከተሞች የነበረውን የስራ አጥነት ችግር ለማቃለል ባለፉ ጠቂት አመታት 14 ሺህ 680 ሰራ አጦች ከ2 ሺህ 9 መቶ በላይ በሚሆኑ የአነሰተኛና ጥቃቅን ተቋማት ተደራጅተው ወደስራ ገብተዋል። ለእነዚህ ማህበራት ከ7 ነጥብ 5 ሚሊየን ብር በላይ ብድር ተሰጥቷል። የመሳሪያ ቦታ እንዲያገኙ ከመደረጉ በተጨማሪ ማህበራቱ ገበያ እነዲያገኙ ሰፊ የገበያ ትስስረ ተፈጥሮላቸዋል።

በቤኒሻንጉል ጉምዘ ክልል ከ1983 ዓ/ም በፊት የነበረው መነገድ 316 ኪሎ ሜትር ብቻ ሲሆን፣ በ2006 ዓ/ም በአምስት እጥፍ አድጎ 1547 ኪሎ ሜትር ደርሷል። ምንም ያለነበረው የገጠር ቀበሌዎችን የሚያገናኝ መነገድ በ2006 ዓ/ም ከ4 ሺህ ኪሎ ሜትር በላይ መድረስ ችሏል።

በትምህርት ረገድ ከ1987 ዓ/ም በፊት አንድ ብቻ የነበረው የክልሉ የአፀደ ሕፃናት ቁጥር አሁን 34 ደርሷል። ከእነዚህ መሃከል 21 ያህሉ የግል ናቸው። ከ1987 ዓ/ም በፊት 189 ብቻ የነበረው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶቸ ቁጥር በ2006 ዓ/ም በሶስት እጥፍ ገደማ አድጎ 526፣ 4 በቻ የነበረው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቁጥር በ12 እጥፍ አድጎ 48 ደርሷል። ከፈተኛ ትምህርትን በተመለከተ ከ1983 በፊት በክልሉ አንድም ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ ያለነበረ ሲሆን፣ አሁን ስድስት የቴክኒክና ሙያ፣ የግብርናና የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች አገልግሎት በመሰጠት ላይ የገኛሉ። ክልሉ የአንድ ዩኒቨርሲቲ ባለቤትም ነው፤ የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ።

የጤና አገልግሎትን በተመለከተ ከ1983 ዓ/ም በፊት 32 ብቻ የነበረው የጤና ኬላዎች ቁጥር በ2006 ዓ/ም ከ 12 እጥፍ በላይ አድጎ 39፣ 3 ብቻ የነበረው የጤና ጣቢያዎች ቁጥር

ደግሞ ከ13 እጥፍ በላይ አደጎ 40 ደርሷል። ከ1983 ዓ/ም በፊት በክልሉ ምንም ሆሰፒታል ያለነበረ ሲሆን አሁን የተለያየ ደረጃ ያላቸው 6 ሆስፒታሎች አገልገሎት በመስጠት ላይ የገኛሉ።

እነዚህ ከላይ የተገለፁ የቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ስኬቶች የህገመንግስቱ ተሩፋቶች ናቸው። እነዚህን ስኬቶች ሁሉም የኢትዮጳያ ክልሎች እጅግ ኋላ ቀር የነበሩት የጋመቤላ፣ አፋር፣ ሶማሌ ክልሎችም ይጋሩታል።

በአጠቃላይ በየአመቱ የኢፌዴሪ ህገመንግስት የፀደቀበት ቀን ላይ - ህዳር 29 የሚከበረው የኢትዮጵያ በሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዘቦች ቀን መድረሻው አንዳንዶች እነደሚያስወሩት ተሰብሰቦ መጨፈር ሳይሆን፣ በኢትዮጳያ በሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዘቦች ላይ ተጭኖ የነበረው ብሄራዊ ጭቆና የተሻረበትና ፓለቲካዊና ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች የተረጋገጡበት፣ ሰላምን በማሰፈን በልማት የህዳሴ ጉዞ አዲሰ ምዕራፍ የተጀመረበት ዕለት የሚዘከረበትና የሚከበርበት ዕለት ነው።

ሁሉም የኢተዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች በበአሉ ላይ የየራሳቸውን ማንነት የሚየንፀባርቅ ትዕይንት ማቅረባቸው ማንነታቸው መከበሩን የመመስከር፣ ባህላቸውን ለሌሎች የማስተዋወቅ ዓላማ ያለው ነው። ይህ የኢትዮጵያ በሄሮች፣ በሄረሰቦችና ህዝቦች በአንድ ቦታ ታድመው የየራሳቸውን ማንነት የሚያንፀባርቅ ትእይንት የሚያቀርቡበት ሁኔታ እንዲሁም በተለያዩ አካባቢዎቾ በተመሳሳይ ሁኔታ በአሉ መከበሩ የአዲሰ አድማስ ጋዜጣ ፀሃፊ ባዩልኝ አያሌው እንዳሉት አንድነትን የሚያናጋ ሳይሆን፤ በመፈቃቀድ፣ በመከባበርና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ በልዩነት ውስጥ ያለ የህዝቦች አንድነትን የሚያጠናክር፣ በመከባበርና በእኩለነት አበረው ለመኖር ያላቸውን ፍላጎት የሚያንፀባርቅ ለዘላቂ የኢትዮጵያ ህልውና፣ ሰላምና እድገት ዋስትና የሚሰጥ በአል ነው።